ይህ ሕግ አንድ ግብር እንዲፈጸም ወይም እንዳይፈጸም አስቀድሞ ማስጠንቀቂያና ምርጫን የሚያደርግ ቢሆን ከተደረገ በኋላ መጥፎ እንደሆነ መፀፀትን ሐዘንን ያመጣል መልካም ከሆነ ደግሞ ደስታን መጽናናትን ይሰጣል፡፡ ማንኛውም የክርስትና ተከታይ የሆነ በስሙ የተጠራ ወገን ሁሉ ፍሊጋውን የሚከተል ሁሉ የራሱን የሕሊና ምርጫ ማክበር የእግዚአብሔርን ድምጽ ምስጋት ግዴታው ይሆናል፡፡ እየተጠራጠረ እያመነታም የሚሰራ ሰው ሁሉ ከሕሊናው ግምት ውጭ ይሠራል ማለት ነው፡፡ ይህም እራስን መበደል ነው፡፡ ሮሜ. 14፣23

በዚህ ምክንያት የሕሊና ዓይን በኃጢአት ምክንያት ይጨልማል፤ ይተኛል፤ ይደክማል፡፡ ግን ፈጽሞ ከነፍስ አይለይም፤ አይጠፋም፤ ምክንያቱም ከነፍስ ጋር የተያያዘ አድርጎ አምላክ የቀረፀውን በነፍስ ያሳደረው በዕውቀት ነውና የሕሊና ፈቃድ አጠራጣሪ በሚሆንበት ጊዜ ማለት መልካም ነው ብለን ፈቅደን አቅደን የፈጸምነው አንዳንድ ጊዜ መጥፎ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ መልካሙ ክፉ መስሎ ይገኛል« ስለዚህ ሳይሠራ ያመለጠ ከሁሉ አስቀድሞ በምንሠራው ሥራ እንደ ኃይማኖታችን ጽናት መጠራጠር አይገባንም፡፡ ይህንን ሁሉ ለማስወገድ ከሁሉ በፊት፣

1. ጸሎት መጸለይ ማለት የሚሠሩትን ሁሉ «ወይኩን ፈቃድከ» ብሎ መጠየቅ
2. ዓላማው ማንኛውም ነገር ከእግዚአብሔር ፍቅር የተነሣ የሱን አምልኮትና ፍቅር መግለጫ መሆን ይኖርበታል፡፡ አምላክ ሰውን አፍቅሮ አንድያ ልጁን ለእኛ አሳልፎ ቤዛ እንደሰጠ ሁሉ ዮሐ. 3፣16
3. ስለ እግዚአብሔር ክብር ተብሎ የሚሠራ መሆን ይኖርበታል፡፡ 1ኛ ቆሮ. 10፣31
4. ስለባልንጀራው ፍቅር መሆን ይገባዋል፡፡

## ዐሥርቱ ትዕዛዛት

ከእግዚአብሔር አምላክ በቀጥታ በሙሴ አማካኝነት ለእስራኤላውያን የተሰጠ ሕግ ነው፡፡ የተሰጣቸውም እስራኤላውያን ከግብጽ ከወጡ በ3ኛው ወር ኒሳን ካከበሩ በ3ኛው ቀን በደብረ ሲና ሰፍረው ሳለ ነበር፡፡ ዘጸ. 19፣1-4 በዘዳ. 34፣28፣ በዘዳ. 4፣13 ላይ አሥሩ ትዕዛዛት አሥር መሆናቸውን እንረዳለን፡፡

በዝርዝር ተጽፈው የሚገኙት ግን በዘጸ. 20፣3፣ 17 እና በዘዳ. 5፣6-21 ላይ ነው፡፡ አሥርቱ ቃላትና ስድስቱ ትዕዛዛት ለእስራኤል ዘስጋና ለእስራኤል ዘነፍስ የተዘጋጁ ስለሆነ ሁላችንንም ይመለከታል፡፡ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፡፡

## ክፍል አንድ

## ዐሥርቱ ትዕዛዛት

1. እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ነኝ ከግብጽ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣሁህ ነኝ ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ ... እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝ፡፡ ዘፀ. 20፣2
2. የእግዚአብሔር የአምላክህን ስም በከንቱ አታንሳ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ ያደረገውን ይቀስፈዋል፡፡ ዘፀ. 20፣7
3. የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ፡፡ ዘፀ. 20፣3-11
4. አባትህንና እናትህን አክብር ዕድሜህ የረዝም ዘንድ እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር፡፡ ዘፀ. 20፣12
5. አትግደል፡፡ ዘፀ. 20፣13
6. አታመንዝር፡፡ ዘፀ. 20፣14

7. አትስረቅ። ዘፀ. 20፥15
8. በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር። ዘፀ. 20፥16
9. የባልንጀራህን ቤት አትመኝ፣ አህያውንም ማንኛውንም ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ አትመኝ።
10. ባልንጀራህን እንደራስህ አድርገህ ውደድ። ዘሌ. 19፥18

እነዚህ ሕግጋት የብሉይ ኪዳን መሠረቶች ናቸው። እግዚአብሔር ሕግን ብትጠብቁ ብትፈጽሙትም ሕዝቤ ትሆናላችሁ እኔም አምላክ እሆናችኋለሁ ብሎ ቃል ኪዳን ገባ። ሕዝቡም በአንድ አፍ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው «እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እናደርጋለን፣ እንታዘዛለን» ብለው ቃል ኪዳን ገቡ፤ ዘፀ. 19፥8፣ 24፥1-8፣ ቅዱስ ጳውሎስም እንደነገረን ይህ ፊተኛው ኪዳን ያለ ደም አልተመረቀምና ዕብ. 18፥22 ሙሴ ኪዳኑን ለማጽናት የደም መርጨት ሥርዓትን እንደአደረገ።

በሐዲስ ኪዳንም ቢሆን ዐሥርቱ ትዕዛዛት ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት ያላቸው ሕግጋት ናቸው። ማቴ. 5፥17፣ 19፥15-22 (ዮሐ. 1፥12 እግዚአብሔር ሕዝቡቹና ልጆቹ ሊያደርገን ይህን ቋሚ ተስፋ በመስጠት ቃል ከገባልን እኛ ደግሞ ትዕዛዙን ለመጠበቅ ምን ያህል ቃል ገብተንለታል? ጌታችን ብትወዱኝስ ትዕዛዜን ጠብቁ ዮሐ. 14፥15 እንዲሁም ከሆነ እንደ እስራኤላውያን እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እናደርጋለን እንታዘዛለን ብለን ከሁሉ በፊት ለእግዚአብሔር ቃል መግባት አለብን። ክርስትናውን ስንጀምር የመጀመሪያ ሥራችን መሆን ያለበት ይህ ነው።)

## የዐሥርቱ ትዕዛዛት ዓላማ

ዐሥርቱ ትዕዛዛት የተሰጡት በሚከተሉት ዓላማዎች መሠረት ነው። ይኸውም፣

1. ከግብጽ ምድር ስላወጣቸው ውለታውን እንዲያስቡ
2. ወደፊት በአረማውያን መካከል ሲመላለሱ ከኃጢአት እንዲጠበቁ
3. መንፈሳዊ አካሄዳቸው ምን ምን አቅጣጫ መከተል እንዳለበት ማሳየት ነው።

ዛሬም ቢሆን እግዚአብሔር ከኃጢአት ዓለም ነፃ አውጥቶናል። ይኸውም በበግ ደም ሳይሆን በልጁ ደም የተፈጸመ ስለሆነ ውለታውን ከልብ ልናስበው ይገባናል።

ስለዚህ ኃጢአትን በሚሠሩ ዓለማውያን መካከል ስንመላለስ ዐሥርቱ ትዕዛዛትን በማክበር እንጠበቅ፤ እንዲህ ከሆነ መንፈሳዊ አካሄዳችን መልካሙን አቅጣጫ የተከተለ ይሆናል ማለት ነው።

## የዐሥርቱ ትዕዛዛት አከፋፈል

1. የክርስቲያን ሕግ የፍቅር ሕግ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ሌላውን የሚወድ ሕግን ፈጽሞታል ካለ በኋላ ከዐሥርቱ ትዕዛዛት የተወሰኑትን በመጥቀስ ፍቅር የሕግ ሁሉ ፍጻሜ መሆኑን በግልጽ ይናገራል። ሮሜ. 13፥8-10 ታዲያ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳስተማረን ፍቅር በሁለት ይከፈላል። ማቴ. 22፥34-41

1. ፍቅረ እግዚአብሔር 2. ፍቅረ ቢጽ

በተጨማሪም ጌታችን ሕግም ነቢያትም በነዚህ በሁለት ትዕዛዛት ተጠቃለዋል ብሎ ስለተናገረ በዚህ ሐሳብ መነሻነት ዐሥርቱ ሕግጋት በፍቅር አከፋፈል መሠረት በሁለት ይከፈላሉ ማለት ነው። ይኸውም እንደሚከተለው ነው።

1ኛ. ፍቅረ እግዚአብሔር ከ1ኛ ትዕዛዝ እስከ 3ኛ ትዕዛዝ ያሉት ሲሆኑ እግዚአብሔርን የሚመለከቱ ናቸው።

በተጨማሪም ጌታችን ሕግም ነቢያትም በነዚህ በሁለት ትእዛዛት ተሰቅለዋል ብሎ ስለተናገረ በዚህ ምክንያት ዐሥርቱ ሕግጋት በፍቅር አክናፈል መሠረት በሁለት ይከፈላሉ ማለትም ነው:: ይኸውም እንደሚከተለው ነው::

1ኛ. ፍቅረ እግዚአብሔር ከ1ኛ ትእዛዝ እስከ 3ኛ ትእዛዝ ያሉት ሲሆኑ እግዚአብሔርን የሚመለከቱ ናቸው::

2ኛ. ፍቅረ ቢጽ ከ4ኛ ትእዛዝ እስከ 10ኛ ትእዛዛት ያሉት ሲሆኑ ባልንጀራን የሚመለከቱ ናቸው::

በሌላ በኩል ደግሞ ከአዎንታዊና አሉታ ከመነገራቸው አንፃር በሁለት ይከፈላሉ፡፡ ይኸውም፣

1. ሕግ በአሉታ የተነገሩ /አታድርግ/
2. ትእዛዝ በአዎንታ የተነገሩ /አድርግ/

ከዚህም ሌላ ከአፈፃፀማቸው አንፃር ሲታዩ በሦስት ይከፈላሉ::

1. በሐልዮ የሚፈጸሙ 1፣ 3፣ 4፣ እና 9 በሃሳብ
2. በነቢብ የሚፈጸሙ 2 እና 8 በመናገር
3. በገቢር የሚፈጸሙ 5፣ 6፣ 7፣ እና10በሥራ ናቸው::

## ዐሥርቱ ትእዛዛትና ጽላት

ዐሥርቱ ትእዛዛት በሙሴ በተሰጡ ጊዜ በሁለት የድንጋይ ጽላቶች ላይ ተጽፈው ነበር:: ዘፀ. 34፣28 እንዲሁም ሁሉ በተለይም እስራኤል ዘነፍስ የምንባለው ለእኛ ለክርስቲያኖች ከልባችን ጽላት ላይ በመንፈስ ልንጽፈው ይገባል:: ኤር. 31፣33 ሕዝ. 36፣26 ዮሐ. 3፣1-3 2ኛ ቆሮ. 3፣1-6

በቤተክርስቲያን በጽላቶቻችን ላይ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይገኛል:: ጌታችን ደግሞ ማንኛውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ ካለ በኋላ ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ ብሎ አስተምሯል:: ዮሐ. 14፣14-15 እንዲሁም ከሆነ የሚያስፈልገንን ነገር ለመለመን የጌታችን ስሙ ስለተፃፈበት በዙሪያው ተሰብሰበን መለመን ያስፈልጋል:: ሁልጊዜም በልባችን የጌታችን ስም ተጽፎልናል ብለን ራሳችንን መጠየቅ አለብን:: በልባችን የጌታችን ትእዛዜን ጠብቁ የሚለው ትምህርት ከልባችን ከለማይጠፋ ሕጉን መጠበቅና መፈጸም ይገባናል:: ለዚህም ዐሥርቱ ትእዛዛትን እያንዳንዳቸውን በዝርዝር ከዚህ ቀጥሎ እንማራለን::

### ፩ ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ

አንድ አምላክ እግዚአብሔር ብቻ ነው:: ከሁሉ በፊት ለዚህ ዓለም ፈጣሪና አስገኝ፣ አሳላፊ፣ መጋቢ አለው:: እርሱም እግዚአብሔር ነው ብሎ ማመን አለበት:: ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ ፈጣሪ መጋቢ የለም:: ፈጣሪ እንደሆነ መዝ. 99፣3፣ ዘፍ. 1፣1፣ ዮሐ. 1፣3፣ ዮሐ. 14፣15፣ መጋቢ እንደሆነ ዘፍ. 1፣29፣ መዝ. 135፣25፣ መዝ. 146፣7-11፣ ማቴ. 6፣25-33 እንዲሁም ከሆነ አምላክ እግዚአብሔር ብቻ ነው:: ኢሳ. 43፣10-13፣ 44፣6-8፣ ትንቢ፣13፣4 ሰው ሌሎች አማልክት የሚመኘው የእውነተኛውን አምላክ የእግዚአብሔርን ሕልውና ሲክድ ነው ስለዚህ የመጀመሪያው ትእዛዝ ሌሎች አማልክትን እንዳናመልክ ብቻ ሳይሆን የእውነተኛውን አምላክ ሕልውና መካድና አምልኮቱን መዘንጋት እንደማይገባ ያስተምረናል:: ኢሳ. 46፣9 አምላክ

ምንም የሚሳነው ነገር የለምና። ዘፍ. 18፤14፤ ሉቃ. 1፤37 ሁሉን ማድረግ ይችላል። እርሱን ብቻ ማምለክ ይገባል። አንድ ነገር ማድረግ እንዳይችል የሚከለክለው ማንም የለም። ዳን. 4፥35፥ ኢሳ. 43፤13 እግዚአብሔር አይለወጥም። ሚል.3፤6 የእግዚአብሔር ምክር ለዘለዓለም ነው። እግዚአብሔር የማያደርገውን አይናገርም የተናገረውንም አያስቀርም ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም። ዘመናት ይቀያየራሉ እግዚአብሔር ግን ያው እግዚአብሔር ነው። አይለወጥም። መዝ.32፤11፤ መዝ.101፤25-28፤ ማቴ.4፤35 ስለዚህ እግዚአብሔር የተናገረውን ቃል የማያስቀር መሆኑን ማመን ይገባናል። ባለፉት ዘመናት የሰራ እግዚአብሔር ዛሬ እንደማይሠራ በማሰብ የራሳችንን አማራጭ አምላክ መፍጠር የለብንም። እግዚአብሔር ትናንትም ዛሬም ወደፊትም ያለ ነው። ዕብ. 13፤8 እግዚአብሔር መንፈስ ነው። ስለዚህ አይወሰንም የሐ.ሥራ. 5፤ ዮሐ. 20። የመጀመሪያው ትዕዛዝ ግን ይህን እንዳናደርግ ይከለክለናል። ይህን ሕግ የሚያፈርሱ ሰዎች ብዙ ዓይነት በደል ይበድላሉ። ይኸውም፣

1. የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር የተባለውን ትዕዛዝ ይለውጣሉ
2. ከቤተክርስቲያን አንድነት ውጭ ይሆናሉ
3. ተስፋ ቢስ ሁሉ የጨለመባቸው ሆነው ይገኛሉ።

ምልክት ከእግዚአብሔር በቀር ለማንም ሊሰጥ አይችልም ደግሞም አይገባም አክብሮትና የፀጋ ስግደት መስጠት ስማቸውንም መጥራት ግን ለመላእክት ለቅዱሳን ሁሉ ልናደርግ ይገባናል። በቅዱሳን ስም ምጽዋት ልንሰጥ በጎ አድራጎት ልንፈጽም እንችላለን። በጸሎትም ስማቸውን ልንጠራ የአማላጅነታቸውን ቃል ኪዳን እንዲፈጽሙልን ልንለምን እንችላለን። ማቴ.10፤41-42

## አምልኮት ዘበፀጋ

መጽሐፍ ቅዱስ ቅዱሳን አማልክት ይላቸዋል። መዝ. 81፤6፤ ዮሐ. 10፤34 ለምሳሌ ሙሴን ለፈርኦን አምላክ አደርጌሃለሁ በማለት እግዚአብሔር ነግሮታል። ዘጸ.7፤1 ከዚህም ጋር ሁላችንም የእግዚአብሔር ልጆች የመሆን ሥልጣን ተሰጥቶናል። ዮሐ.1፤12፤ራዕ.3፤21. በቤተክርስያናችን ቅዱሳንን እናከብራለን ይኸውም ከመጀመሪያው ትዕዛዝ ጋር የሚያጋጭ አይደለም። የእግዚአብሔርን አክብሮት አምልኮት ለቅዱሳን አንሰጥምና እንድያውም ለእነርሱ የምንሰጠው ክብር እግዚአብሔርን ማክበር ስለሆነ በብዙ ምስጋና ለእግዚአብሔር እናቀርባለን። 2ኛ ቆር. 9፤13 ስለዚህ ቅዱሳንን ማክበር ከእግዚአብሔር ውጭ ልዩ አምልኮት አለመሆኑን መገንዘብና ማስገንዘብ ያስፈልጋል።

## ሌሎች አማልክት የተባሉ

ሰው እንደ እግዚአብሔር የሚያያቸውና ብቸኛውን የእግዚአብሔርን ባሕርይ የሚሰጣቸው ነገሮች ሁሉ አምላክ ሊሆኑ ይችላሉ።

1. ገንዘብ ማቴ. 6፤24፤ 19፤22 የሐ. ሥራ. 5፤1
2. የሰው ኃይል ኤር. 17፤5
3. የሰው ጥበብ ዕውቀት ኤር. 9፤23
4. ሆድ ራስ ወዳድነት ፊል. 3፤19
5. የምንታመንባቸው ሰዎች መዝ.145፤3 አለቆቻችን፣ ወገኖቻችን የሐ. ሥራ. 5፤29

## ሌሎች አማልክት የትባሉ

ሰው እንደ እግዚአብሔር የሚያያቸውና ብቸኛውን የእግዚአብሔርን ባሕርይ የሚሰጣቸው ነገሮች ሁሉ አምላክ ሊሆኑ ይችላሉ።

1. ገንዘብ ማቴ. 6፣24፣ 19፣22 የሐ. ሥራ. 5፣1
2. የሰው ኃይል ኤር. 17፣5
3. የሰው ጥበብ ዕውቀት ኤር. 9፣23
4. ሆድ ራስ ወዳድነት ፊል. 3፣19
5. የምንታመንባቸው ሰዎች መዝ.145፣3 አለቆቻችን፣ ወገኖቻችን የሐ. ሥራ. 5፣29
6. አባትና እናት ማቴ.10፣37
7. ኒማኒጥ ዘፍ. 35፣2-4
8. ተድላ ደስታ 2ኛ ጢሞ. 3፣4
9. የተቀረፀ ምስል ዘጸ. 20፣4፣ የሐ. ሥራ. 10፣1-16፣ ጠንቋይ፣ ሟርተኛ፣ ቃልቻ፣ መናፍስት ጠሪ 1ኛ ሳሙ.28፣3-19፣ ኤር.29፣8፣ የሐ.ሥራ. 13፣6-12፣ የሐዋ.ሥራ.16፣16-18

## አይሁንልህ /አታምልክ/

አምላክ ሲባል እምነትን ተስፋን ፍቅርን በአምላክ ላይ መጣል ነው። እምነቱን ተስፋውን ፍቅሩን ከእግዚአብሔር ላይ አንስቶ በሌሎች አማልክት ላይ ሲጥል ነው ሌላ አምላክ አመለከ የሚባለው። ሌሎች አማልክትም አይሁንልህ ሲባል እምነትና ተስፋ ፍቅር ከእግዚአብሔር በቀር በሌሎች ላይ አይሁኑ ማለት ነው። አምልኮት በተግባር የሚውለው በሚከተሉት ነገሮች ነው።

1. ዐስግደት 2. መስዋዕት 3. ጸሎት 4. ውዳሴ 5. መገዛት 6. ፍርሃት ወዘተ

በመጀመሪያው ትዕዛዝ መሠረት እነዚህን ነገሮች ከእግዚአብሔር በቀር ሌሎች አማልክት ማድረግ ተገቢ አይደለም። አለመከተልና አለማምለክን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን ማምለክ በሚደረገው ኅብረት አምልኮ በግል በምንፈጽመው ለእግዚአብሔር ታዛዥነታችንን ልንገልጽ ይገባናል። ኢሳ. 44፣5 እግዚአብሔርን እያመለኩ በሌላ በኩል ሌላ አምላክ መከተል ደግሞ እጅግ የከፋ ኃጢአት ነው። በኤልያስ ጊዜ 3 ዓመት ከመንፈቅ ድርቅ የሆነው የባሊዕን ምርኮ የሆነው በዚህ ኃጢአት ምክንያት ነው« 1ኛ ነገ. 18፣16-24፣ ኤር.11፣9-14 ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ ከእግዚአብሔር በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ ሲል ሌሎች አማልክትን ማቴ. 6፣24 ስለዚህ እንግዶች አማልክትን አስወግደን በሕይወታችን ላይ እግዚአብሔርን ገዥ ልናደርገው ይገባናል። ዘፍ..35፣2

## በማናቸውም ምሳሌ የተቀረጸውን ምስል ለአንተ አታድርግ

ይህን ሁለተኛ ትዕዛዝ የሚያደርጉት አሉ። እኛ ግን በአንደኛው ትዕዛዝ እናጠቃልለዋለን።

## የተቀረጸ ምስል

የተቀረጸ ምስል ማለት አንድ ቅርጽ ሠርቶ ይህ አምላክን ይመስላል ወይም አምላክ ነው ብሎ የሚሞለክ ምስል ነው። ይህ ጣኦት ይባላል። በዚህ ትዕዛዝ መሠረት የማናቸውንም ምስል ሲል የተቀረጸ ምስል በሦስት ይከፈላል። ይኸውም

1. በላይ በሰማይ ባለው ነገር የተቀረጸ ምስል ምሳሌ ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት፣ የሚበሩ አዕዋፍ ወ..ዘ..ተ
2. በታች በምድር ባለው የተቀረጸ ምስል ምሳሌ በወንድ መልክ፣ በሴት መልክ፣ በእንስሳት መልክ።
3. ከምድር በታች በባሕር ውስጥ ባሉ ነገሮች የተቀረጸ ምስል ምሳሌ በዓሣ፣ በጉማሬ፣ አዞ፣ ወ.ዘ.ተ

ዘዳ..4፣10-19 ተመልከት የተቀረጸ ምስል ወይም ጣኦት በሚከተሉት ነገሮች ሊሠራ ይችላል«.

1. በማዕድን /ወርቅ፣ ነሐስ፣ ብረት፣ ብር/ በማስቀረጽ ዘጸ. 34፣17፣ ኢሳ.30፣22
2. እንጨት በመጥረብ ኢሳ. 40፥20
3. ድንጋይ በማለዘብ ምስል ቀርጾ ጣኦትን ማምለክ የአሕዛብ /የአረማውያን ልማድ ነው። ነገር ግን እስራኤልም ቢሆኑ ከግብጽ ምድር ያወጣቸውን አምላክ እግዚአብሔርን በመዘንጋት ብዙ ጊዜ ጣኦትን አምልከው እንደነበር የሚከተሉት ጥቅሶች ያስረዳሉ። ምሳ.2፣11-14፣ 2ኛ ነገ. 17፣7-18 21፣11-12 1ኛ ነገ.12፣25-32

በዚህ በአንደኛው ትዕዛዝ እኔ እግዚአብሔር አምላክ ቀናተኛ ነኝ በማለት እግዚአብሔር እንዳስረዳው ሰው ለእጁ ሥራ ሲንበረከክ በተመለከተ ጊዜ ዝም ብሎ አልተመለከተም ብዙ ጊዜ ይቆጣ ነበር ዛሬም ቢሆን የእግዚአብሔር ቅጣት እንዳይሰነዘር የተቀረጹ ምስሎችን ማራቅ አለብን።

## ለአንተ አታድርግ

ለአንተ አታድርግ የሚለው ትዕዛዝ አነጋገር አትስገድላቸው፣ አታምልካቸው በሚለው ቃል ተብራርቷል ዘጸ. 20፣5። አሕዛብ ጣኦትን ሲያመልኩ በኮረብታዎች መስዋዕትን በመሰዋት ዕጣንን በማጠን ወደ እነርሱም በመጸለይና በመስገድ አካላቸውን እንኳ ሳይቀር በመጉዳትና በማሰቃየት ነበር። ይህ ትዕዛዝ እንዲህ እንዳናደርግ ያዝዘናል። በአንጻሩም ደግሞ እግዚአብሔር ሕጉ የተጻፈበትን ጽላት ማደሪያ የሆነውን የእንጨት ታቦት እንዲቀርጹ ያዘ መሆኑን መዘንጋት የለብንም። ዘጸ. 38፣18፣ 34፣1-25፣ 40፣20 የኪሩቤል ቅርጽም ከተቀጠቀጠ ወርቅ እንዲሠራ በመጋረጃው ላይ እንዲሰሩ አዟል። ዘጸ. 25፣12-22 ይህ ሲባል ጽላቱና ታቦቱ የኪሩቤል ቅርጽም እግዚአብሔር አምላክ ሆነ ወይም እግዚአብሔር አምላክን መስለው የሚመለኩ ሳይሆን እግዚአብሔር በሚመለክበት ጊዜ ለቅዱስ አገልግሎት የሚውሉ ንዋያት ቅድሳት ናቸው። የእግዚአብሔር የክብሩ መገለጫዎች ናቸው። ዛሬ በቤተክርስቲያን ያለው ጽላትና የስዕል ጉዳይ ከዚህ ጋር የሚታይ ነው። በታቦተ ጽዮን የሚገለጠው እግዚአብሔር መሆኑን በአሕዛብ ሀገር እንኳ ታውቋል። በታቦተ ጽዮን ዳጎን የሚባለው ጣኦት እንደተሰባበረ ይታወቃል። 1ኛ ሳሙ. 5፣1-5 ስለዚህ የእግዚአብሔር ታቦት /ማደሪያ/ የሆነው ሰውነታችን ጣኦታትን መሰባበር ብሎም ማቃጠል ይገባዋል። ሰውነታችን መቅደስ ነው የእግዚአብሔር ቤተመቅደስም ከጣኦት ጋር ምንም ኅብረት ስለሌለው 2ኛ.ሳሙ. 6፣14 ከጣኦት መለየት ይገባል። ጣኦትን የሚያመልኩት ለጣኦት የሚሰው ለአጋንንት ይሰዋሉ። ታዲያ ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን የተቀበለ ሰውነት የአጋንንትን

መስዋዕትን በመሰተፍ ከአጋንንት ጋር ማኅበርተኛ መሆን የለብንም። 1ኛ ቆሮ. 10፥16-22 የተቀረፀ ምስልን /ጣኦትን/ ማምለክ ጣኦት ኃይል የሌለው ከልካይ የሰው እጅ ሥራ ምንም ማድረግ የማይችል መሆኑን እንድናስተውል ይሆናል። ኢሳ. 44፥18 ጣኦት ግን ዓይን እያላቸው የማያዩ ጆሮ እያላቸው የማይሰሙ እግር እያላቸው የማይራመዱ እንደእነሱ ስለሆነ ከዚህ ለመዳን ከጣኦት ሽሹ ራሳችሁን ጠብቁ ይለናል። 1ኛ ቆሮ.10፥14፣ 1ኛ ዮሐ. 5፥2

## 2ኛ ትዕዛዝ

## የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ

### የእግዚአብሔር ስም

ስም ሲባል አንድ ነገር ከሌላው ተለይቶ የሚታወቅበት መጠሪያ ነው። ስም ጠባይን ግብርንና ሁኔታን እንደሚገልጥ ሆኖ ሊሰየም ይችላል። እግዚአብሔርም ባሕርዩን ሕልውናውን ግብሩን የገለጹ ብዙ ስም አለው። ዘጸ 15፥3፣ አሞጽ. 4፥13 ከብዙዎቹ የእግዚአብሔር ስሞች ሦስቱን እንደሚከተለው እንመለከታለን።

1. ኤል ኃያል ማለት ነው። ዘፍ.. 17፥1
2. ኤሎሄ አምላክ ማለት ነው። ማቴ. 27፥46
3. ያሕዌ ያለና የሚኖር ማለት ነው። ዘፍ. 22፥4፣ ዘጸ.3፥13-15 ዘጸ.17፥15 ክርስቶስ እርሱ እግዚአብሔር ነው። በሐዲስ ኪዳን እግዚአብሔር ወልድ በሥጋ ሲገለጥ በሚከተሉት ስሞች ተጠርቷል።

1. አማኑኤል ኢሳ. 7፥14 ማቴ. 1፥23
2. ኢየሱስ ማቴ. 1፥25 ሉቃ. 1፥31
3. ክርስቶስ

የእግዚአብሔር ስም ባዶ ቃል አይደለም። ኃይሉን ግርማውን ይዞ ይገኛል። ማቴ. 18፥20 የማይታየው እግዚአብሔር ራሱን የገለጠው በስሙ አማካኝነት ነው። በተለይም ክርስቶስ በሥጋ በተገለጠ ጊዜ ስሙን ለዓለም አስታውቋል። ዮሐ. 17፥26 ስሙም ከሁሉ በላይ ነው። ፊል. 2፥9-11 «ዕግዚእ መባልን፣ አምላክ መባልን፣ ወልድ መባልን ሰጠው»

ሕዝቡ ሁሉ እያንዳንዱ በየአምላኩ ስም ይሄዳል እኛም በአምላካችን በእግዚአብሔር ስም ለዘለዓለም እንኖራለን። ሚክ. 4፥5 ስለዚህ የእግዚአብሔርን ስም አክብረን ልንይዘው ልንቀድሰው ይገባል እንጂ በከንቱ ልንጠራው አይገባም። ስሙ ቅዱስ ነውና ሉቃ.1፥50 እስራኤል በሐሰት መማል ያበዙ ነበር። እግዚአብሔር የእውነት አምላክ ስለሆነ በእውነት እንጂ በሐሰት መማል ሊጠራ አይገባም። የእግዚአብሔር ስሙ በከንቱ የሚጠራ ከበደሉ ሊነፃ አይችልም። በሐዲስ ኪዳን ጌታችን እንዲያ የእግዚአብሔር ስም በከንቱ መጥራት ለራስ መማል እንደማይገባ አስተምሯል። ማቴ. 5፥34-39

መላእክት ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉ የሚያመሰግኑት አምላክ መሆኑን አውቀን ስሙን በከንቱ መጥራት ግብሩን ማርከስ ነው። ሌላው ደግሞ ጌታ አምላክን በአፍ እያመሰገኑ በልባቸው

ውስጥ አምቀው ስሙን የሚጠሩ አሁንም ስሙን ከንቱ ማድረግ ነው። እምነት በአፍም በልብም ነውና ሮሜ. 10። በማኅበር ስንኖር ከሳሽ ተከሳሽ ስለሚኖር የክርክሩ መፈጸሚያ የእውነት ማረጋገጫ መሐላ ስለሆነ ጽኑው እንዲምል ካስገደደው መማል ይፈቀዳል። ዘጸ. 22፣11 ዕብ. 6፣13። ከዚህ ሌላ ቃል ለመግባት አንድ ነገርን ለመሥራት መሐላ ሐሳል ቃል መስጠት የእግዚአብሔር ስም መጥራት የሚያስፈልግባቸው ጊዜ አለ። እንዲሁም እግዚአብሔርን ለማገልገል ሲሉ ብፅዓት የሚያደርግ አለ ይኸም በቤተክርስቲያን ሥርዓት የተፈቀደ ሥርዓት ነው። ለምሳሌ በድንግልና ለመኖር።

## በከንቱ አትጥራ

ከንቱ ማለት በእግዚአብሔር የተናቀ የማይገባ ምናምን ነገር ማለት ነው። የእግዚአብሔርን ስም በእንዲህ አይነት ሁኔታ መጥራት እንደማይገባ ይህ ትዕዛዝ ያስተምረናል። የሚከተሉት ነገሮች ከንቱ እንደሆኑ መጽሐፍ ቅዱስም ያስተምረናል።

1. የሰው ሥጋዊ ፈቃድ ኢዮብ 7፣3 መዝ. 38፣5-6፣ ሮሜ 8፣20፣ ኤፌ. 4፣17
2. ጣኦትን ማምለክ 2ኛ ነገ. 17-15፣ ኢሳ. 44፣9
3. ሐሰተኛ ትንቢት ሕዝ. 13፣1-23 ዘካ. 10፣1 2ኛ ጴጥ. 2፣18 በእነዚህ ከንቱ ነገሮች የእግዚአብሔርን ስም መጠቀም ስሙን በከንቱ መጥራት ነው። ይኸውም፦
4. በእግዚአብሔር ስም በሐሰት መማል ዘካ. 5፣4 ማቴ. 5፣33-37
5. በእግዚአብርሔር ስም መራገም ማቴ. 5፣44 ሮሜ 12፣14
6. በእግዚአብሔር ስም መጠንቆል ኢሳ. 19፣3 የእግዚአብሔር ስም ማቃለልና ክብር አለመስጠት ስሙን ከንቱ ማድረግ ነው። ምሳሌ በእግዚአብሔር ስም ለተቀደሱት ነገሮች ክብር አለመስጠት ዳን. 5፣23-26
7. በእግዚአብሔር ስም የተናገርነውን ቃል አለመፈጸም። ዘጸ. 23፣21-23 በስሙ ወይም ስለስሙ የምናስተምረውን በተግባር አለማዋል። ሮሜ. 2፣24 ቲቶ. 1፣16 ይህ ትዕዛዝ ብርቱ ማስጠንቀቂያ የያዘ ስለሆኑ በማስተዋል ልንጠብቀው ይገባል።

የእግዚአብሔርን ስም የምንጠራው ምን ጊዜ ነው?

1. በጸሎት ጊዜ። ኢዮ. 2፣32 ዮሐ. 14፣14
2. በሰላምታ ጊዜ ጴጥ. 1፣1-2፣ ሮሜ. 1፣7
3. በአምልኮ ጊዜ መዝ. 134፣3፣ ት.ሚል. 1፣11፣ ፊልጵ. 2፣10
4. በቡራኬ ጊዜ ዘኁል. 6፣23፣ 2ኛ ቆሮን. 13፣13

## 3ኛ ትዕዛዝ

## የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ

የቃሉ ትርጉም አቆመ አረፈ ማለት ነው። ይህ ማለት የሰው ልጅ ከጌታ ጋር የሚቀራረብበት መገናኛ መንገድ ነው። ከማንኛውም ሥጋዊ ተግባር የምናርፍበት፣ ትርጓሜው የእግዚአብሔርን ሥራ እንድናስታውስ የሚያደርግበት ቀን ነው።

ይኸውም በቅዱስ መጽሐፍ ተጽፏል። ሰንበት የመንግሥተ ሰማይ ምሳሌ ነች። የሰው ልጅ በዓለም ሠርቶ ወጥቶ ወርዶ በመልካም ሥራው የሚያርፍበት ቦታ ናት። ሰው ዕረፍት ያስፈልገዋል የሰንበት ቀን የተፈጠረውም ለዚህ ነው። ዘጻ. 5፣14፣ ማር. 2፣28

የሰንበት ቀን ከሥነ ፍጥረት ጀምሮ የታወቀ ነው። እግዚአብሔር ስድስት ቀን ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን አርፎአል። ዘፍ. 2፣2-3 ለዚህ ትዕዛዝ መነሻ የሆነው ይኸው ነው። የሰንበት ቀን የዕረፍት ቀን ስለሆነ የሚከተሉት ሁለት ነገሮችን ያሳስበናል።

1. ሰው በኃጢአት ከመውደቁ በፊት ከአምላኩ ጋር ያለውን ግንኙነት የነበረውን ዕረፍት

2. ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት የተገኘውን ዘለዓለማዊ የነፍስ ዕረፍት ዕብ. 4፣1-10 በሐዲስ ኪዳን ሰንበት ሁለት ናቸው ቀዳሚትና እሑድ። ቅዳሜ፣ ማለት የበፊቷ የቀደመችው ማለት ነው። ቆላስ. 2፣1

<u>እሑድ፣</u> ማለት ደግሞ መጀመሪያ ስለሆነ ከዚህ ጀምረን ስንቆጥር ቅዳሜ በባተኛ ቀን ይሆናል። በዚህ 3ኛ ትዕዛዝ እንዲከበር የታዘዘው ይህ ቀን ነው። ይህ ቀን እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብጽ ባርነት ወደ እረፍት እንዳወጣቸው ያመለክታል። ዘዳ. 5፣2-16 በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ዘንድ ምልክት ነበር። ዘፀ. 31፣17፣ ሕዝ. 20፣12 እስራኤላውያን ሰንበትን በጥብቅ ያከብሩ ነበር ሰንበትን አለማክበር ግን ከባድ ቅጣት ያስከትል ነበር። ዘኁ. 15፣32-36 ሰንበትን የማያከብሩ ሰዎችንም በነቢያት ይወቅሱ ነበር በባቢሎን ምርኮ ጊዜ ተዛብቶ በአንዳንዶችም ተረስቶ የነበረውን በነቢዩ ነህምያ አማካይነት በሙሴ ሕግ መሠረት እንዲከበር ተደረገ። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እና ሐዋርያት ይህን ቀን አክብረውታል። ሉቃ. 4፣16 ፈሪሳውያን በሰንበት ቀን እግር ከዘረጉ አያጥፉም፣ ከአጠፉም አይዘረጉም መልካምም ሥራ ቢሆን አይሠሩም ነበር። ማቴ. 12፣1-14

<u>ከማምንቱ በፊተኛ ቀን</u>

ይህ ቀን ዛሬ እሑድ የምንለው ቀን ነው። ይህ ቀን ሥነ ፍጥረት የጀመረበት ኋላም ጌታ የተነሳበት መንፈስ ቅዱስ የወረደበት እንዲሁም ጌታችን የሚመጣበት ዕለት ነው። የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ይህን የመጀመሪያ ቀን ልዩ ትኩረት በመስጠት ይሰበሰቡበት ነበር። ስለዚህ ቀን ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚከተለውን እንረዳለን።

ሀ. ጌታ እንደተነሳበት ዮሐ. 20፣1-24

ለ. መንፈስ ቅዱስ እንደወረደበት የሐዋ. ሥራ. 2፣1-4

ሐ. የጢሮአዳ ምእመናን እንደሚሰበሰቡበት የሐዋ.ሥራ 20፣7

መ. ገንዘብን እንደሚያዋጡበት 1ኛ ቆሮ. 16፣2

በቤተክርስቲያን ታሪክ ደግሞ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ዕለተ እሑድ የክርስቲያኖች ቀን ስለሆነች ሥራ እንዳይሠራ እንደወሰነ ይተረካል። ይኸውም ማለት በሕገ መንግሥቱ አጽድቆ አውጆአል ማለት ነው እንጂ በክርስቲያኖች ዘንድ ዕለተ እሑድ ከጥንት ጀምሮ የሚታወቅና የተከበረ ዕለት ነው። በብሉይ ኪዳን ከፋሲካ በፊት የሰንበት ማግስት በመባል በኩራትና ቀዳምያት የሚቀርብበት ቀን ነው። ራዕ. 1፥10 ክርስቶስ በዚህች ቀን ከሙታን ተነስቶ ሠላምና እረፍት ሰጥቶናል። እሑድ የሰንበት ትርጉምን የሚያሟላ ስለሆነ ይከበራል።

**ሰንበትን ማክበር**

የሰንበት ቀን የዕረፍት ቀን ስለሆነ የሰው ልጆች እረፍት እንድናገኝ ስድስት ቀን በሥራ የደከመው ሰውነታችን እንዲታደስ እግዚአብሔር የሠራልን ትዕዛዝ ነው። ስለዚህ ሥጋዊ ፈቃዳችንን በዚህ በተቀደሰው ቀን ከማድረግ በመከልከል ሰንበትን ማክበር አለብን። ኢሳ. 58፥13 እኛ በሰንበት ከመሥራት ተከልክለን ሠራተኞቻችንንም ሆነ እንስሶቻችንም እንድናሰራ አልተፈቀደም። ዘዳ. 5፥14 የሰንበት ቀን ከሥራ ተከልክለን የምናርፍበት ቀን ብቻ ሳይሆን ባልተከፈለ ልቡና እግዚአብሔርን የምናመልክበት ቀን ነው። እንዲያውም የዚህ ትዕዛዝ ዋናው ቁም ነገር ይህ ነው። ስለዚህ ቀን የትግባር ዕረፍት ነው ስለተባለ ሥራ ፈትን መዋል የለብንም። በተቀደሰው የእግዚአብሔር ገባዔ መገኘትና እግዚአብሔርን ማምለክ ቃሉን በመማር ከእግዚአብሔር የሚገኘውን ሰላምና እረፍት መቀበል አለብን። ዘሌ. 23፥3

ከዚህም ሌላ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰንበት መልካም ሥራ መሥራት ተፈቅዷል ብሎ ባስተማረው መሠረት መልካም ሥራ በመሥራት እናከብራታለን። ምሳሌ ጌታችን በዚህ ቀን በሽተኞችን ይጎበኝና ይፈውሳቸው ነበር። ማቴ. 12፥12 እኛም በሽተኞችን፣ የታሠሩ ሰዎችን መጠየቅ ይገባናል። ወደቤተክርስቲያን በመሄድ መባዕ በማስገባት ለድሆች ምጽዋት መስጠት የተጣሉ ሰዎችን ማስታረቅ ይገባል። በመንፈሳዊ ጉባዔያት ሁሉ መገኘት የእግዚአብሔርን ቃል መስማትና ለእግዚአብሔር ዝማሬን ማቅረብ ተገቢ ነው። ለነፍሳችን ዕረፍት የምናገኘው ከክርስቶስ ነው ጌታችን ወደ እኔ ኑ ከእኔም ተማሩ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ ይላል። ማቴ. 11፥28 ስለዚህ ዘላለማዊ ዕረፍት የሆነው ክርስቶስ ከእኛ ጋር ይኖራልና ዮሐ. 6፥56 እንግዲህ በክርስትና ሰንበት የሚከበረው በዚህ መልክ ነው። የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል። ዕብ. 4፥11 ከዚህ ሌላ በቅድስት ቤተክርስቲያን ሥርዓት መሠረት ወር በገባ ቁጥር የሚከበሩ ዕለታት አሉ። በ12 ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል በ21 የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም በ29 በዓለ ወልድ ናቸው።

## 4ኛ ትዕዛዝ

## አባትህንና እናትህን አክብር

አባትህንና እናትህን አክብር የሚለው ትዕዛዝ የፍቅረ ቢጽ መጀመሪያ ነው። አራተኛው ትዕዛዝ ወላጆቻችንን እንድናከብር ያዝዛል። ዘፀ. 2፥12 በዘፀአት እንደተጠቀሰው ሁሉ በአዲስ ኪዳንም ከሌሎች ትዕዛዛት ጋር ተጠቅሷል። ማቴ. 15፥4፣ ማቴ. 19፥18፣ ኤፌ. 6፥1 አባትና እናት ቢል በሥጋ የወለዱንን ብቻ ሳይሆን በአርአያ ሥላሴ የተፈጠሩ ሁሉ እንድናከብር ነው። እነዚህም የሥጋ አባቶችና የመንፈስ አባት በማለት ለሁለት ከፍለናቸዋል።

**1. የሥጋ አባት**

ሀ. ወልጆቻችን ዕብ. 12፥9፣ ዘፍ. 2፥24

ለ. ያትውልድ አባት ዮሐ. 4፥12

ሐ. የአንድ ዓይነት የኑሮ ወገን አባት ዘፍ. 4፥20

መ. አሳዳጊ/ሞግዚት/ 1ኛ. ቆሮ. 4፥15

ሠ. በወላጆቻችን ዕድሜ የሚገኙ

ረ. የቀለም አባቶች

ሰ. የሀገር መሪዎች ሮሜ. 13፣7፣ 1ኛ ጴጥ. 2፣17ተ. የቤት አባት

ሸ. ሽማግሌዎች ዘሌ. 19፥32፥ 1ኛ ጴጥ. 1፥2 በ. የእንጀራ አባት

፪. የመንፈስ አባትና እናትዋ

ሀ. የንስሐ አባት ለ. ካህናት

ሐ. የወንጌል ሰባኪ 1ኛ ቆሮ. 4፥15፥ 1ኛ ጢሞ. 5፥17፥ 1ኛ ተሰሎ. 5፥12

መ. ቅዱሳን አባቶች እና እናቶች ጸን. 7፣27

ሠ. የክርስትና አባትና እናት

## አክብር

አባት እና እናት ማክበር ማለት መውደድ፣ መታዘዝ፣ መርዳት፣ አለማቃለል ማለት ነው። ዘሌ. 19፣3፣ ዘጻ. 27፣16፣ ቆላ. 3፣20 በሁሉ ለወላጆቻችሁ ሲል በሁሉ የሚለው ቃል ብዙ ነገሮችን ያመለክታል። ይኸውም፣

ሀ ምክራቸውን በመስማት ምሳ. 1፣8፣ 1ኛ ሳሙ. 2፣25

ለ. በተቸገሩ ጊዜ የሚያስፈልጋቸውን በመስጠት ዘፍ. 4፣12

ሐ. በሌላቸው ጊዜ የሚረዱበትን መንገድ ማዘጋጀት ዮሐ. 19፣26-27

መ. በጠቅላላው ለወላጆች ብድራትን መመለስ 1ኛ ጢሞ. 5፣4

ወላጆችንም ሆነ ሌሎችን የሥጋና የመንፈስ አባቶችን ሲኖራቸውም፣ ሲያጡም፣ ጤና ቢሆኑ፣ ቢታመሙም፣ ባረጁ ጊዜ ልንረዳቸው ልናከብራቸው ልንሰጣቸው ይገባል። አቅም አግኝተን ወላጆቻችንን የምንረዳ እኛ ብንሆን እንኳን ማክበር እንደሚገባን ጌታ አስተምሮናል። ማቴ. 15፣1 ምሳሌ 22፣23 ሲራ. 3፣11 ይህንና ወላጆቻችንም ሆነ ሌሎች ከእግዚአብሔር ጋር የሚያጣላና የሚያጋጭ ትዕዛዝ ነው። ቢያዙን ከእግዚአብሔር ይልቅ እነርሱን ብቻ መውደድም ማክበርም አይገባም። 1ኛ ሳሙ. 20፣31፣ ማቴ. 10፣35-37፣ ማቴ. 19፣22

በተገቢው መንገድ ግን አባትና እናትን ማክበር ዕድሜን እንደሚያረዝም አራተኛው ትዕዛዝ ያስተምረናል። ዘፀ. 20፣22፣ ኤፌ. 3፣1-3 ከዚህ ሌላ ወላጆቻችንም ሆነ እግዚአብሔርን ያስደስታል። ምሳ. 23፣25፣ ቆላ. 3፣20 ቅዱስ ጳውሎስ ይህ በእግዚአብሔር ፊት መልካምና የተወደደ ነው ብሎታል። አባትና እናትን አለማክበር በብሉይ ኪዳን ያስቀጣ ነበር። ዘፀ. 21፣15፣ ዘዳ. 21፣18-21 ዛሬም ቢሆን አባቱና እናቱን የማያከብረውን እግዚአብሔር ይቀጣዋል። አባትና እናቱም ቢሆኑ ልጆቻቸውን በጌታ ምክርና በተግሳፅ እንዲያሳድጓቸው እንጂ በከንቱ እንዳያበሳጯቸው አራተኛው ትዕዛዝ አይፈቅድም ኤፌ. 6፣4፣ ቆላ. 3፣21 የእግዚአብሔርን ቃል የሚሰማ ልጅ እናቱን ያሳርፋታል። ባሮቹ ለርሱ እንዲገዙለት እሱም ለወለደው ለአባቱ ይገዛል... ሲራ. 3፣9-10 የአባት ምርቃት የልጅ ቤት ያድናል የእናት እርግማን ግን መሠረት ይነቅላል።

## 5ኛ ትዕዛዝ

## አትግደል፣ ዘፀ. 20፣13

ሕይወት በአጋጣሚ፣ በልማድና በእንዝሕላልነት የምትገኝ አይደለችም። ሕይወት ከአንድ ትልቅ ሕይወት ካለው የተገኘች ነች። ሕይወት ለራሱ ምክንያት እና አስገኝ ከሌለው የተገኘች

ገንዘብ ነች። ሕይወትን ማንም ሊያዝባት እንደፈለገው ሊያደርጋት አይችልም። ለምን? የእርሱ አይደለችምና ለዚህ ነው አትግደል የተባለው በመሠረቱ ሞትን ሰው በገዛ ፍላጎቱ ያመጣው ስለሆነ ሞት ከእግዚአብሔር ያልመጣ እንደሆነ እናውቃለን። በዚህ ሁኔታ ማንም ሰው ነፍስ ማጥፋት የለበትም። ዘፍ. 9፣6፣ 1ኛ ነገ. 20፣19 ስለናቡቴ።

<u>መግደል</u>፣ ማለት በተለያዩ መንገድ ተጠቅሞ የሰው ሕይወት እንዲሞት ማድረግ ነው። መግደል ከውስጥ ከሰው የሚወጡ ሰውንም የሚያረክሱ ብሎ ጌታችን ከዘረዘራቸው ክፉ ሥራዎች አንዱ ነው። ማቴ. 15፣19፣ ማር. 7፣22 ቅዱስ ጳውሎስም በገላትያ ላይ ከዘረዘራቸው 16 የሥጋ ሥራዎች አንዱ መግደል ነው። ገላ. 5፣21 በሕይወት ላይ ሥልጣን ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ዘዳ. 32፣32-39 ብሎ እንደተናገረ ሰውን ቢያድንም ቢገድልም ሥልጣኑ የእግዚአብሔር ነው። ነገር ግን በትዕቢት ተነሥቶ አንድ ሰው እንደራሱ የተፈጠረውን ሌላ ሰው ቢገድል ከባድ ኃጢአት መሆኑን ይነግረናል። መግደል ሲባል ፊት ለፊት ሄዶ የሰውን ሕይወት ማጥፋት ብቻ ሳይሆን ሰውን ለሞት የሚያበቁትን ነገሮች ሁሉ ነው።

ይኸውም፣

- በተለያዩ ሁኔታ (በቃላትና በመጠቆም) አጥፊውን መርዳት
- የሰው ሕይወት ሊድን የሚችልበትን መረጃ በመከልከል
- በሽታና ድካምን ሌላም ችግርን ሲያዩ ለሞት የሚያደርስ ሥራ ማሰራት
- ለሞት የሚያደርስ ረሀብንና ጥም በሽታም አይተን የተቻለንን አለመርዳት
- ሰውን በሥጋ ብቻ ሳይሆን በነፍሱ መከራ የሚያመጣበትን መንገድ መፍጠር መግደል ነው።
- ግለማውያንን በመንፈስ ባዶ ቀፎ ሆነው የተበላሸብትን ወደ እናት ቤተክርስቲያን አለማምጣት ነፍስን መግደል ነው።

## ወደ <u>መግደል የሚያደርሱ ነገሮች</u>

ወደ መግደል የሚያደርሱ ብዙ ነገሮች አሉ እነርሱም ቅንዓት፣ ምቀኝነት፣ ስድብ፣ ጥላቻ፣ ቁጣ ጥቂቶቹ ናቸው። ከነዚህ ውስጥ ቁጣን በንመለከት በሁለት ሰዎች መካከል የሚነሳው ጠብ የሚያባብስ ዋነኛ ምክንያት ነው። በእርግጥ የሚገባ ቁጣ አለ ይህንንም ሲያስረዳ ተቆጡ ነገር ግን ኃጢአትን አታድርጉ መዝ. 4፣4፣ ኤፌ. 4፣25 ጌታችን «አትግደል» የሚለው ሕግ ለመፈጸም በቅድሚያ ወደ መግደል የሚያደርሰውን ቁጣን ማስወገድ እንዲገባ ሲገልጽ... «በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል» በማለት ገልጾታል። ማቴ. 5፣21-22

## አትግደል ሲባል ምን ያመለክታል?

ይህንን ትዕዛዝ በሐዲስ ኪዳን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ጳውሎስ፣ ቅዱስ ያዕቆብ ከተወሰኑ ትዕዛዛት ጋር አብረው አንስተውታል። ማቴ. 19፣18፣ ሮሜ. 3፣9፣ ያዕ. 2፣11 መግደል የሥጋ ሥራ በመሆኑ ነፍስ ገዳዮች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም። ዘጸ. 24፣16፣ ማቴ. 5፣21 የሰዎች ደም በከንቱ ፈሶ አይቀርም እግዚአብሔር የአቤልን የደሙን ድምፅ ሰምቶ ቃየንን እንደተበቀለ ይበቀላል። ዘፍ. 4፣9-15 በቀል የእኔ ነው ብድራትን እመልሳለሁ ብሎ ጌታ ስለተናገረ ሰዎች ችግር እንኳን ቢደርስባቸው በቁጣ ተነስተን ራሳችን እንድንበቀል

አልተፈቀደም። ሮሜ 12፥19 ነገር ግን በሕጋዊነት አጥፊዎችን በሞት ለመቅጣት ለባለሥልጣኖች ተፈቅዷል። ዘዳ. 21፥18-23 የሐ. ሥራ 13፥6-12 ይሁን እንጂ እነርሱም ቢሆኑ ከሕግ ውጪ ሰውን ለሞት አሳልፈው መስጠት አይችሉም። አትግደል የሚለው ትዕዛዝ በመንፈሳዊ ትርጉም ሲታይ የሰውን ሞራል በመንካት አትግደል ነው። ሰውየው እያየው እየታወቀው ስለሆነ ሞራሉን የሚመታው ቃል መናገር ቀላል መናገር ቀላል ኃጢአት አይደለም።

ከዚህ ሌላ ሰውን ከእግዚአብሔር እንዲለይ እንዲርቅ ማድረግ እንደማይገባ ትዕዛዙ ያሳስበናል። ምክንያቱም ሰው ከእግዚአብሔር ከተለየ መንፈሳዊ ሕይወቱ ይሞታል። ኃጢአትም ይሠራል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው። ሮሜ. 6፥23። ስለዚህ በሐሰት ትምህርት በዓለማዊ ስብከት ሰዎችን ከእግዚአብሔር እንዲርቁ ማድረግ ነፍሰ ገዳይ መሆን ነው። ዲያብሎስ «እርሱ በመጀመሪያም ነፍሰ ገዳይ ነበር።» የተባለው በዚህ ምክንያት ነው ዮሐ. 8፥44። የእግዚአብሔር ቃል በእኔ ከሚያምኑ ከነዚህ ከታናናሾች አንዱን የሚያሰናክል ሁሉ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባሕር መስጠም ይሻለው ነበር። በማለት ያስተምረናል። ማቴ. 18፥6

ራሳችንን እንደምንወድ ሁሉ ሌላውን መውደድ ይገባናል። መሞት እንደማንፈልግ ሌሎችንም የሚሞቱበትን መንገድ ማዘጋጀት የለብንም እንደራሳችን እንጠነቀቅላቸዋለንና። ወንድሙን የሚጠላ እርሱ ነፍሰ ገዳይ ነው ተብሏል። 1ኛ ዮሐ 3፥15 ክርስትና ራሳችንን አሳልፈን በመስጠት ለሌላው እንድንሞት እንጂ ሰውን በጥላቻ እንድንገድል አያስተምረንም። ዮሐ. 15፥12 ጥላቻም ቢሆን በንግግር ይገለጣል። በተለይ ደግሞ በሸንገላ ፍቅር ሰዎችን በማቅረብ ጥላቻን መግለጽ መግደል ነው። ይህ የእባብ ጠባይ ነው። መጥምቁ ዮሐንስና ጌታችን የአብርሃም ልጆች ነን እያሉ ሲመኩና ሲታበዩ የነበሩትን እናንተ የእፉኝት ልጆች እባቦች በማለት ይወቅሷቸው ነበር። ማቴ. 3፥7

አትግደል ሌላውን ብቻ ሳይሆን እራሳችንንም ጭምር ነው። በራሳችንም ላይ ሥልጣን ያለው እግዚአብሔር ነውና። ዘፍ. 5፥9 በተለያዩ ነገሮች የራሳችንን ሕይወት በመታነቅ፣ ባሕር ውስጥ በመግባትም፣ መርዝ በመጠጣት፣ በጥይት በመምታት በተጨማሪም በሚከተሉት መንገዶች ነፍስን ማጥፋት ፈጽሞ በእግዚአብሔር ዘንድ የተከለከለ ነው። በስካር፣ በሱስ፣ በጫትና በሲጃራ፣ በዝሙት፣ ጽንስን በማስወረድ ልጅ እንዳይወለድ መከላከያ በማድረግ መግደል ነው።

## 6ኛ ትዕዛዝ

### አታመንዝር

ይህ ትዕዛዝ ስለማንኛውም ሰው ክብር፣ ንጽህና፣ ቅድስና ሕይወት ሲባል ተዘጋጅቷል። ይህ ሕግ ለምድራዊ ኑሮአችን መመሪያ ይሆን ዘንድ የተሰጠ ነው።

ይህ ትዕዛዝ ጾታዊ ሕይወትን የሚመለከት ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ ከሌላው አረማዊ ሕዝብ የተለየ ወይም ቅዱስ መሆን ስለሚገባው በጾታ ሕይወቱ ላይ ሕግ ተሰጥቶታል። የጾታ ሕይወት በተቀደሰ ጋብቻ ተጠብቆ በጥንቃቄ ከተያዘ ቅዱስና ደስ የሚያሰኝ ሕይወት ነው« ከዚህ እንዳንወጣ ሕግ የተሰጠን ለምድራዊ ኑሮአችን እንጂ በረቂቁ ዓለም ግን ማግባትና መጋባት

2. **ሴሰኝነት፣** እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት በጋብቻ ተወስኖ ቤተሰብ ለማፍራት የማይፈልግና እራስ ወዳድነትን ስግብግብነት የሚያጠቃው ሰው ሴሰኛ ይባላል።

3. **አመንዝራነት፣** ባል ሚስቱን ትቶ ወይም ሚስትም ባልዋን ትታ፣ ቤትዋን ትታ፣ ጋብቻዋን ዘንግታ ከሌላ ወንድ ጋር እና ከሌላ ሴት ጋር መሄድ አመንዝራነት ይባላል። ይህ አመንዝራነት በስህተት አይፈጸምም ማለት ሁኔታን አጥንቶ ሰልሎና አስቦ ተዘጋጅቶ የሚደረግ ነገር እንጂ እንደ እንቅፋት ጉድጓድ የሚወደቅበት አይደለም። ጨለማን ለብሶ ሰው አየኝ አላየኝ ተብሎ የሚሠራ ሥራ ነው።

## የአመንዝራነት መንሥኤ

መንስኤ ማለት የአንድ ነገር መነሻው መሠረቱ ምንጩ ማለት ሲሆን፣ የአመንዝራነትንም መንስኤዎችን ማወቁ ይጠቅማል። እነዚህም፣ መጠጥ፣ ፊልም፣ የምንዝር ጌጥ፣ አደንዛዥ ዕፅ፣ የወሲብ መጽሐፍት፣ ጭፈራ ወዘተ....

ሀ. ሐሳብ፣ ጠግቦ መብላት ለ. ምኞት ሐ. አለባበስ መ. መነጋገር፣ መቀራረብ መተያየት ሠ. መላፋት፣ መተቃቀፍ ወዘተ.... በሌሎችም ነገር ሁሉ ቅዱስ የነበረውን ሰውነት ያረክሱታል። አንድ ሴት ከ3-4 ድረስ ካገባች አመነዘረች የተፈታችዋንም ያገባ እንዲሁም አንድ ወንድ ከ2-3 ሴት ካገባ አመነዘረ ይህም ትልቅ ዘማዊነት ነው። የተፈታችም ማግባት ማመንዘር ነው። ማር. 10፣2 እያንዳንዱ ወንድ የራሱ ሚስት ትኑረው ሴትም ባል ይኑራት 1ኛ ቆሮ. 7፣2

## የአመንዝራነት ፍጻሜው በሦስት ይከፈላል

1. የአእምሮ/ሞራል/ ሞት፣ ወኔ ማጣት ለሥራ እንቅስቃሴ ማጣት
2. የመንፈስ ሞት፣ የላሸቀና ባዶ ይሆናል ትንሳኤ ልቡና ያጣል
3. የሥነ ምግባር ሞት፣ በሰው የተጠላ ሬብ የሌለው መጠቋቆሚያ መሆን። ዝሙት ሞትን ያመጣል። 1ኛ ቆሮ. 6፣6-9 በአራት ሕግም ዘማዊ ሰው በድንጋይ ተወግሮ ይሙት ይባላል።

## የአመንዝራነት መንፈሳዊ ገጽታ

ኃይማኖት መለዋወጥ ዝሙት ነው። ማቴ. 12፣38 በየጊዜው ጓደኛን መለዋወጥ ወረተኛነት በአንድ አለመወሰን የማያገኙትን መሻት፣ መመኘት ከእግዚአብሔር ሌላ ወደ ጣዖት መሄድ ማመንዘር ነው።

## ግብረ ሰዶም መሥራት

ይኸም ዝሙት ሲሆን በበለጠ ከተመሳሳይ ጾታ ጋር የሚደረግ የረከሰ ግንኙነት ስለሆነ እንስሶች እንኳን የማይሠሩትን ሥራ የሰው ልጅ ስለሚሠራው በደሉ ቅጣቱ አሁንም ከፍተኛ ነው። በጥንቱ ዘመን ግብረ ሰዶም ማለት ወንድ ከወንድ ጋር የሚያደርጉት ግንኙነት ነበር። በዘመናችን ግን ሴቶችም ከሴቶች ጋር የሚያደርጉት ግንኙነት አላቸው ይኸም /ሊዝቢያኒዝም/ ይባላል። ሮሜ. 1፣24-27 ወንዱ የምትሆነውን ሴት ማግባት ሴቷም የሚሆናትን ወንድ ማግባት በብሉይም በሐዲስም የተፈቀደ ቅዱስም የሆነ ግንኙነት ነው። በዚህም ምክንያት የሰው ዘር ይበዛል። ጤንነቱም ይጠበቃል። የኑሮ ጸጥታን ያገኛል። ጋብቻም በእምነት ከብሯል። 2ኛ ቆሮ. 6፣9

## 7ኛ ትዕዛዝ

## አትስረቅ

ሰው ሁሉ ያልደከመበትን ንብረት እንዳይፈልግ የራሱን ብቻ ሠርቶ እንዲጠቀም አንዱ በሌላው ጉልበት እንዳይኖር ጉልበተኛ አቅመ ደካማውን እንዳያጠቃ ሁሉም ተስማምቶ እንዲኖር ይህ ሕግ ተሰጠ።

እያንዳንዱ ሰው የግሉን ድርሻ ንብረቱን መጠበቅና መንከባከብ አለበት። የሰውን ሕይወት የምንንከባከብባቸው በሕግ የተሰጡ ሦስት ነገሮች አሉ።

1. ሕይወት 2. ጋብቻ 3. ንብረት ናቸው

ሰው የግል ድርሻ ከሌለው ሕይወቱ ለስርቆት ይጋበዛል። የግል ድርሻ መጠበቅ ባይኖር ኖሮ ዓለም ዝብርቅርቅ፣ ውጥንቅጡ የጠፋ ሕይወት ይኖረው ነበር። ሰው የራሱ ንብረት ሊኖረው ይገባል።

<u>የመስረቅ ምክንያቶች ምንድን ናቸው?</u>

1. ዋናው ምክንያት አለማመን ነው
2. እግዚአብሔርን አለመፍራት
3. ምኞት
4. በሰይጣን ግፊት በመነሳሳት አትስረቅ የሚለው ይህ ትዕዛዝ በሐዲስ ኪዳን ጌታችን በድጋሚ ጠቅሶታል። ማቴ. 19፣18

የሰው ንብረት እንዲጠበቅ አትስረቅ ያለው ሕግ ተሰጠ። በዘሌዋውያን ላይ «አትስረቅ» ተብሎ ተነግሯል። ዘሌ. 19፣11 በዚህ ትዕዛዝ እግዚአብሔር ሰው ያልደከመበትንና የራሱ ያልሆነውን ንብረት በማናቸውም ምክንያት ያለባለንብረቱ ፈቃድ እንዳይወስድ ያሳስባል።

<u>ስርቆት፤</u> ስርቆት ያለባለቤቱ ፈቃድ የሌላውን ንብረት መውሰድና መጠቀም ነው። ሰውንም ከሚያረክሱት የኃጢአት ዓይነቶች አንዱ መስረቅ ነው። ማቴ. 15፣19 አንድ ሰው የሚሰርቀው በሚከተለት ምክንያት ነው።

- ምንም ስለሌለው በድኅነት፣ በችግር
- በተንኮልና በምቀኝነት
- በልማድ

ይህንና በምንም ምክንያት ይሁን ስርቆት ነው። ስርቆት በሚከተሉት ዓይነት ሊፈጸም ይችላል።

1. በመቀማት
2. ባለቤቱ ሳያውቅ በስውር በመውሰድ
3. በማታለልና በማስመሰል

ስርቆት እግዚአብሔር የሚጠላው ስለሆነ የሚሰርቁም የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም ሲል ቅዱስ ጳውሎስ ተናግሯል።

አትስረቅ ሲባል የግል ንብረትና ገንዘብ መሆኑን ያመለክተናል። ስለዚህ በዚህ ሕግ መሠረት አንድ ሰው ያልሠራውንና ያልደከመበትን የሌላውን ሰው ንብረት፣ ገንዘብ ያለባሌቤቱ ፈቃድ መውሰድ አይችልም። ሰውን መስረቅ ከመግደል ያላነሰ ኃጢአት ነው። ምክንያቱም ተቸግሮ በመራብ ወይም ተበሳጭቶ በመታመም የተሰረቀው ሰው ሊሞት ይችላልና ነው። ነገር ግን አትስረቅ የሚለው ትዕዛዝ በቀጥታ ብቻ ሳይሆን በተዘዋዋሪም የሚፈጸሙትን ስርቆት ይከለክለናል። ለምሳሌ፥ በንግድ ቦታ በሚዛን በመበደል፥ የማይፈለግ ዕቃን አስመስሎ በመሸጥ ስርቆት በሥራ ቦታም የሥራ ሰዓትን አለማክበር ባልሰሩበት ሰዓት ገንዘብ መቀበል ስርቆት ነው።

የሠራተኛን ዋጋ ቀንሶ መክፈል ስርቆት ነው። ያለጊዜ መግባት መቀበልም ስርቆት ነው። በዚህ ዓይነት በተዘዋዋሪ የሚፈጸሙ ስርቆቶች ሕግን ያስታውሱ በማስተዋል እንመለከታቸው ይገባል። በእግዚአብሔር ስምና ቃል እያሰበኩ የምእመናንን ንብረት ለግል መጠቀም ሌብነት ነው። ጻፎችና ፈሪሳውያን በጸሎት ርዝመት እያመካኙ የመበለቶችን ቤት ይበሉና ይበዘብዙ ነበር። ማቴ.23፣14፡ ሉቃ. 20፣47 ይሁዳም ለድሆች ያሰበ መስሎ ማርያም በቢታኒያ ጌታን የቀባችውን ሽቶ «በሦስት መቶ ዲናር ተሸጦ ለድሆች ያልተሰጠ ስለምን ነው ያለው ሌባ ስለነበር ነው።» ዮሐ 12፣3-6 ዛሬም ቢሆን አትስረቅ ብለው የሚያስተምሩ በጉን በተዘዋዋሪ አስመስለው የሚሠርቁ ከሆነ ከይሁዳም አይለዩም። «አትስረቅ ብለህ የምትሰብክ ትሰርቃለህን?» ይላል። ሮሜ.2፣21 ከዚህ ሌላ አትስረቅ ሲባል ሰውን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርንም እንዳንሰርቀው ያሳስበናል። የእግዚአብሔርን ጊዜ ሠርቀን የምናገኘው ገንዘብ በስርቆት እንደመጣ ይቆጠራል። ባንሠራበትም እንኳን የእግዚአብሔርን ጊዜ መሰረቅ አይገባም። ከአሥር አንድ ለእግዚአብሔር እንድንሰጥ ታዟል። ስለዚህ ከምናገኘው ከአሥር አንዱ የእግዚአብሔር ነው። ለግላችን ከተጠቀምንበት ግን ስርቆት ነው። «ሰው እግዚአብሔርን ይሰርቃልን? እናንተ ግን እኔን ሰርቃችኋል።» ሚል.3፣8 በተጨማሪ ስዕለትን ተስለን ሲሳካልን ስዕለቱን አለማቅረብ ስርቆት ነው። ለግላችን እንጠቀምበታለንና የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር እንድንሰጥ እንጂ ልንሰርቅ አይገባንም። እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ የግል ንብረትን የሰጠው ለራሱ የሚበቃውን ከተጠቀመ በኋላ ለሌላው ይሰጣል እንጂ አይሰርቅም። የእግዚአብሔር ቃል «ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው።» ይላልና።

የሐዋ.ሥራ 20፣35 ይህን ለማድረግና ከስርቆት ለመዳን በገዛ እጅ ጠንክሮ መሥራት ይገባል ቅዱስ መጽሐፍም የማይሠራ አይብላ ይላል 1ኛ ተሰ. 4፣12፡ 2ኛ ተሰ. 3፣10 ከዚህ ሌላ ደግሞ ለኑሮ ያህል ሠርቶ ካገኙ ኑሮዬ ይበቃኛል ማለት ይገባል። ፊል. 4፣12 ሠርቶ ትንሽ ካገኙ በኋላ ወደ ስርቆት የሚገፋፋው በቃኝ አለማለት ነው። «የእግዚአብሔር ቃል ያላችሁ ይበቃችኋል ይላል።» ዕብ. 13፣5 አትስረቅ የሚለው ትዕዛዝ ሰዎች እንዳይሠርቁ ብቻ ሳይሆን የሚሰርቁም ስርቆታቸውን አቁመው እንዲመለሱ ይጋብዛል። «የሰረቀ አይስረቅ» ተብሎ ተጽፏል። ኤፌ. 4፣28 ስለዚህ ማንኛውም ሰው በማናቸውም ዓይነት ምክንያት መስረቅ አይገባውም። የሰረቁ ከስርቆቱ ተመልሰው በገዛ እጃቸው እየሠሩ እንዲኖሩ ለኑሮአቸውም የሚበቃቸውን እንዲያገኙ ይገባል።

## 8ኛ ትዕዛዝ

## በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር

ይህ ትዕዛዝ በማናቸውም ቦታ ጊዜ እንዲሁም በማናቸውም ምክንያት ባልንጀራችን ላይ በሐሰት እንዳንመሰክር ልጓም ሆኖ ይይዛል እግዚአብሔር ይህን ትዕዛዝ የሰጠው የሰዎች በማቸው ክብራቸው ሕይወታቸው እንዲጠበቅ ነው።

ትዕዛዙ ዳኞች ከሳሾችን ምስክሮችን ይመለከታል የሰውን ክብርና መልካም ስም የሚነካ ስለሆነ ክብራችንን ለመጠበቅ ለምስክርነት መቅረብ ብዙ ፈተና አለው። ሐሰት በምላስ ሐሰት በጽሑፍ ሐሰት በፊርማ ሐሰት በዝምታ ሰርቆ በማተም የሐሰት ማስረጃን በመስጠት ይፈጸማል። እግዚአብሔር አምላክ ሰውን ሁሉ አክብር ይላልና። 1ኛ. ጴጥ 2፣17

## በሐሰት አትመስክር

በሐሰት መመስከር ማለት ያላዩትንና ያልሰሙትን ጉዳይ የማያውቁትንና ያላጣሩትን ነገር በትክክል እንዲሚያውቁት አድርገው መናገር መመስከር ነው። በሌላ በኩል ደግሞ

ምሥጢር ከሆነ ነገር በቀር እውነትን አለመናገር አለመግለጽም በሐሰት እንደ መመስከር ይቆጠራል።

በሐሰት መመስከር በተለያዩ ምክንያቶች የሚፈጸም ሰዎችን የማቃለያ መንገድ ነው። ሰዎች በሐሰት የሚመሰክሩ በምን ምክንያት ነው?

- በይሉኝታ
- በዘረኝነት — ቤሰብ ባልደ ... ማሰየት፣ ድሃና ባለጠጋን ማጣላት፣ አባትና ልጅን
- በጥቅም — ማረጋገጥ ወንድምና ወንድምን ማጋደል። ማቴ. 10፥21
- በምቀኝነት
- ምስጋና በመፈለግ/ውዳሴ ከንቱን/
- በልማድ ..... ወዘተ ምክንያት ሊሆን ይችላል።

በሐሰት የሚመሰክር ሰው በሥጋውም በነፍሱም ብዙ ጉዳት አለው። በሐሰት ሰው በአንድ ጊዜ 3 ነገሮችን ይተላለፋል።

1. በሐሰት መመስከሩ ራሱን ይጎዳል ዘጸ. 19፥16-20
2. በሐሰት የተመሰከረበትን ሰው ይጎዳል ምሳ. 25፥18
3. የሚመሰክርለትን ሰው ይጎዳል 1ኛ ነገ. 20፥22-25

ከዚህም ሌላ በሐሰት መመስከር ሌሎች ትእዛዛትንም የሚሽር ከባድ ኃጢአት ነው። ምክንያቱም ሐሰትን በመሐላ ለማጽናት ሲሞክር የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ መጥራት ይሆናልና። በሐሰት የተመሰከረበትን ሰው ሞት ሊፈረድበት ይችላል። ወይም ካሣ ተጠይቆ ገንዘብና ንብረት ሊበዘበዝ ይችላል። በዚህ እኳንን የእግዚአብሔር ስም በከንቱ አትጥራ፣ አትግደል፣ አትስረቅ የሚሉት ሕጎች ሁሉ ይፈርሳሉ። ስለዚህ ሐሰተኛነት ከባድ ወንጀል ነው። ምሳ. 26፥12

ክርስቲያን እውነትን መመስከር አለበት እንጂ የሐሰት በርያ መሆን የለበትም። ስለሰው የምናውቀው ጥቂት ስለሆነ ከሐሰት ምስክርነት እንቆጠብ። በሐሰት የጓደኛን፣ የጎረቤትን፣ የመሥሪያቤትን ስም፤ በየአደባባዩ መናገር በሐሰት ማንሳት ኃጢአት ነው። እውነተኛ የክርስቲያን ፍቅር በግልጽ መናገር ነው እንጂ ማማት፣ መቶቸት አይገባም።

**ይህንን ትእዛዝ ለመጠበቅ፤**

**1. በንግግራችን እውነተኛ ሆኖ መገኘት**

በሥራ ልናሳይ መቻል አለብን። በሃሳብም እውነተኛ በመሆን በሐሰት የተፈረደበትን ማጽናናት ነው። እውነት ከእግዚአብሔር፣ ሐሰት ግን ከዲያብሎስ ነው። ሐሰት ተናጋሪ የሰይጣን የግብር ልጅ መሆኑንም ማወቅ አለብን። ዮሐ. 8፥44 ክርስቶስ በትምህርቱ እውነትን እውነት ሐሰትን ሐሰት እንድንል አስተምሮናል። ማቴ. 5፥37 ሐሰተኛ ከንፈር በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ ነው። ምሳ. 12፥19 የሐሰተኛ ሰው ዕድሉ የዲን እሳትን የተመሰለ የሞት ሞት ነው። ራእይ 21፥8 ውሸታም ሰው፤ ክብር የለውም በሚናገረውም ሐሰት ሲቀል ይኖራል። «ውሸታም ሰውና ስንቅ እያደር ይቀላል።» ቅዱስ ጴጥሮስም መልካም ዘመን ሊያይ የሚሻ ምላሱን ከክፉ ይከልክል ብሏል። 1ኛ ጴጥ. 3፥10፤ መዝ. 33፥2-16።

<u>ሐሰተኛ ነቢያት</u>

በተለየም የሐሰት ዓላማ ተነሳስቶ በሐሰተኛ ሕልምና ራዕይ ወይም በሐሰተኛ ትንቢት እንዲሁም ስብከት ሰዎችን ማታለል ይህንንም ትዕዛዝ ማፍረስ ነው። እግዚአብሔርም በሐሰት የሚመሰክሩትን አይፈልግም። ሰዎችን በሐሰተኛ ሕልምና ራዕይ እንዲሁም ትንቢትና ስብከት የእግዚአብሔርን ሥም ለመጠቀሚያ ፈልገው ያታልሉብታል። እንደዚህ ያሉ ሰዎች ሐሰተኛ ነቢያት እንደሚነሱ አስቀድሞ ክርስቶስ ተናግሯል ማቴ. 24፥14-26። እግዚአብሔር ጥንት በብሉይ ኪዳን ሲያደርግ እንደነበረው ሐሰተኛ ነቢያትና ሐሰተኛ ምስክሮችን ይቃወማል። ዘዳ፡ 18፥20። 2ኛ ዜና 18፥22፤ ኤር. 14፥14። ክርስቲያን ግን በእውነት ለእውነተኛ አምላክ እንደ ሐዋርያት ምስክርነት ሊሰጥ ይገባል። እግዚአብሔር ሐሰትንና ሐሰተኛ ከንፈሮችን በጣም አድርጎ ይጠየፋል። እውነትን የሚያደርጉ ግን በእርሱ ዘንድ የተወሰዱ ናቸው። ምሳ. 21፥22 ሐሰትን የሚናገሩትን ግን እግዚአብሔር እንደሚያጠፋቸው ቃሉ ይናገራል መዝ. 5፥6፤ ምሳ. 21፥23። ስለዚህ ውሸትን አስወግዳችሁ እርስ በርሳችሁ ብልሆች ሆናችሁ እያንዳንዳችሁ ከባልንጀሮቻችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ ኤፌ. 4፥25 ስለሆነም ክርስቲያን በማናቸውም ቦታ በማናቸውም ምክንያት እውነትን መናገር እንጂ ሐሰትን መናገር አይገባውም።

## 9ኛ ትዕዛዝ

## የባልንጀራህን ቤት አትመኝ ዘፀ 20፥17

የሰውን ንፅህና በውጭ ብቻ ሳይሆን በውስጥም መሆን አለበት አትመኝ ሲባል መመኘት ብቻ ሳይሆን አታስበው አትፈልገው ሲል ነው። እግዚአብሔር የእያንዳንዱን ሰው ሕይወት ከልቡ በመነጨ ግዴታ ብቻ ሳይሆን ከሕሊና ከመነጨ ፈቃድ እንዲጠብቅለት ይፈልጋል። ሰው ሕግን እንዲፈራ ብቻ ሳይሆን በሕሊና እንዲያመዛዝን እንዲያገናዝበውም ጭምር ነው። ምኞት ጸንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች፣ ኃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች። ያዕ. 1፥14 ስለዚህ ምኞት ቀላል ኃጢአት ስላልሆነ በአጭሩ መቅጨት ያስፈልጋል። እንዲህ ያለ ኃጢአት ባይሠራም እንደ ተፈጸመ የሚቆጠር ነው። ጊዜና ቦታ አልፈቀዱም እንጂ ከታሰበ ተሰራ ማለት ነው። ሕጉም የተሰጠው በዚህ ምክንያት ነው። ነገር ግን ምኞትን በውጫዊው ማስወገድ ሳይሆን ከምኞት ጋር ታግሎ ማሸነፍን ያመለክታል። ሰዎች በዘሙት ኃጢአት የሚወድቁት አትመኝ የሚለውን ትዕዛዝ በቅድሚያ ሲተላለፍ ነው። ጌታችን ግን ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛት ያን ጊዜም በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሯል። በማለት መመኘት እራሱ አመንዝራነት እንደሆነ ገልጿል። ማቴ. 5፥28። ምኞቱን የገደለ ክርስቲያን ግን አመች ሁኔታዎችን እንኳን ቢሟሉለት እንደ ዮሴፍ ይህንን ክፉ ሥራ በእግዚአብሔር ፊት አላደርገውም ብሎ የዝሙትን ጦር ይሸሻል። ዘፍ. 30፥7-18 በሌላ በኩልም ሰርቆትን፣ ግድያን፣ በሐሰት መመስከርን፣ ፍርድ ማዛባትን የሚፈጽሙት ገንዘብን ሌላም ጥቅምን አላደርገውም ብሎ የዘሙትን ጦር ይሸሻል። አንዳንዶችም ሐይማኖታቸውን። የእግዚአብሔር ሰው ግን ከዚህ መሸሽ አለበት። 1ኛጢሞ. 6፥9-11 ምኞት ብዙ ጉዳት ያለበት ኃጢአት ነው። መልካምን ሊመኝና ሊያስብ የሚገባውን ሕሊና ክፉውን በመመኘት ጊዜውን እንዲያሳልፍ ያደርጋል። እንዲህ የሚያደርግ ሰው ከነፍሱ ጋር የሚታገል ሰውን ይመስላል። 1ኛ ቆሮ. 14፥9-10 ስጋውንና ነፍስን ይጎዳል ክፉ ምኞትን መርምሮ ከተረዳ በኋላ ከሕይወቱ ማስወገድ አለበት። እግዚአብሔርንም የዓመት ልብስ የእለት ጉርስ ስጠኝ ብሎ በጾም በፀሎት በስግደት መማፀን ይገባዋል። ቅዱስ ጳውሎስም ፊተኛው ኑሮአችሁን እያሰባችሁ እንደሚያታልል ምኞት የሚጠፋውን አሮጌውን ሰውነት አስወግዱ ይለናል። ኤፌ. 4፥22 ስለዚህ በምድር ላይ ያሉ ብልቶቻችንን ገድለን ከክርስቶስ ጋር ተሰቅለን ለኃጢአት ሳንሞት ክርስቶስም በውስጣችን ሕያው ሲሆን ክፉ ምኞትም ያን ጊዜ ይወገዳል ቆላ. 3፥5። ገላ. 2፥20 ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምኞት አዳምንና ሔዋንን ንጉሥ ዳዊትንና ሌሎች አባቶቻችንን አሳስቷል።

ሰው ስማይን ያዘል ጸቦ ከሰጠሁ ከዋክብትን ያህል በላተኛ ይወርድብሃል፡፡ ምኞት ወደ ምግባር እንዳለወጥ የሚገፋፋ አወዳደቅን የማያሳምር ኃጢአት ነው፡፡ የሥጋም ፈቃድ ነውና ሞትን ያመጣል፡፡ ሮሜ 8፣12፡፡ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አትመኙ ያለው ከፉውን እንጂ ደጉን አይደለም፡፡ ማቴ. 6፣33፤ 1ኛቆሮ. 14፣1 ክፉ ሃሳብ መጥፎ ምኞት በሰው ላይ የሚሰለጥነው ሰውየው ሥራ ፈት ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ እንግዲህ ሥራ መፍታት እራሱ በደል ነው፡፡ ሥራ ያጣ መነኩሴ ቆቡን ቀዶ ይሰፋል እንዲሉ፡፡

<u>የባልንጀራ ቤት</u>

የባልንጀራ ቤት ሲባል ቤቱን ብቻ ሳይሆን በቤቱ ውስጥ ለኑሮው አስፈላጊ የሆኑትን ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ ይሄንንም በአራት ክፍል ማየት ይቻላል፡፡ ዘፀ 20፣17

1. የባልንጀራ ሚስት
2. ሎሌውን ገረዱንም /አገልጋዩንም/
3. አህያውን፣ በሬውን /እንስሳቱንም/ እነዚህን መመኘት እንደማይገባ ይህ ትእዛዝ ያስገነዝበናል፡፡ ምኞት ከፍ ባለ ስሜት አንድን ነገር መሻትና መፈለግ ነው፡፡ ሰው የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ ለማየት ቢመኝ የቃሉን ወተት ሲመኝ ሰላምን ፍቅርን ሕብረትን ሲመኝ ተገቢ ነው፡፡

<u>10ኛ ትእዛዝ</u>

<u>ባልንጀራህን እንደራስህ አርገህ ውደድ ዘሌ. 19፣18</u>

ባልንጀራ በጣም ስውር ምሥጢር የምንነግረውና እንደራሳችን አድርገን የምንወደው ነው፡፡ በአጠቃላይ ደቂቀ አዳም መዋደድ አለበትና ሁሉንም እንደበጎ ባልንጀራና ወዳጅ ማየት አለብን፡፡ ከአንድ ግንድ የበቀለ ነውና፡፡ ፍቅር፣ ውዴታ፣ ይቅርታ፣ ሰላም፣ አንድነት፣ ረቂቅ አእምሮ እና የሐሳብ ሙጫ ናቸው፡፡ በሐዲስ ኪዳን ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተናገረው በሁለት ትዕዛዛት ሕጉም ሁሉ ነቢያትም ጸንተዋል ማቴ. 19፣17-19፡፡ ማቴ. 22፣34-40 ሁለተኛውም ባልንጀራህን እንደነፍስህ ውደድ የሚለው ነው፡፡ ባልንጀንህን የሚመለከት ትዕዛዛትን የሚያጠቃልል ነው ማለትና አታመንዝር፣ አትግደል፣ አትስረቅ፣ በውሸት አትመስክር፤ አትመኝ የሚለው ከሌሎች ትዕዛዛት ጋር በዚህ ቃል ተጠቅሏል፡፡ ሮሜ. 13፣19

ከዚህም በላይ እግዚአብሔር የምንወደው የምናየውን ባልንጀራችንን በመውደድ ስለሆነ ሕግ ሁሉ በአንድ ቃል ይፈጸማል፡፡ ባልንጀራህን እንደራስህ አድርገህ ውደድ በሚለው የባልንጀራ ፍቅር ሲባል ሌላውን የምንወድበት ፍቅር ነው፡፡ እግዚአብሔር እንደራሱ ይወደናል እና እኛ ደግሞ ባልንጀራችንን እንድንወድ ይገባልና፡፡ 1ኛ ዮሐ. 4፣20 ባልንጀራችን ማን ነው? ባልንጀራችን የሰው ዘር ሁሉ ነው፡፡ ይህም በሉቃስ ወንጌል 10፣29-37 መልስ አግኝቷል የእግዚአብሔር ቃል "እንግዲያስ ጊዜ ካገኘን ለሰው ሁሉ ይልቁንም ለሃይማኖት ቤተሰቦች መልካም እናድርግ" ይላል፡፡ ገላ. 6፣10 በክርስትና ትምህርታችን ሰዎች ሁሉ በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ ተፈጥረዋል፡፡ ሁሉም ከአዳም እና ከሔዋን ዘር የተገኙ ናቸው፡፡ እንዲህ ከሆነ ለሁሉም እኩል የሆነ አንድ ዓይነት ፍቅር ሊኖረን ይገባል፡፡ ሁላችንም ግብዝነት በሌለው እውነተኛ ፍቅር ከልባችን አጥብቀን ልንዋደድ ይገባል፡፡ ሮሜ. 12፣9፤ 1ኛ ጴጥ. 1፣22 የክርስቲያን ፍቅር ከጠባያዊ ፍቅር የተለየ መሆን አለበት ማንኛውም ጠባያዊ ፍቅር መነሻው ምንጩ ቅጥር ሊኖረው ይችላል፡፡ የሚወደንን ብንወድ ከአሕዛብ ምንም ብልጫ የለንም ባልንጀራን መውደድ ሲባል ጠላትንም መውደድ መሆኑን ያጠቃልላል፡፡

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተግባር አሳይቶናል ምሳሌም ሆኖናል። ማቴ. 5፡43-48፤ 1ኛጴጥ፡ 2፡23፤ ሉቃ. 23፡24 ጠላትን ይቅር ብሎአል ብንወደው እንዲሁ በጎ ነው እንጂ ምንም መነሻ አይኖረንም። እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ከወደደን እኛ ደግሞ በአድንን ዘመድንን የቅርቡንም የሩቁንም ወዳጅንም ጠላትንም ቢሆን በአንድ ፍቅር መውደድ ይገባናል። ዮሐ. 3፡16፤ ሮሜ 5፡10 ለባልንጀራችን ያለን ፍቅር የልብ ስሜት ብቻ ሆኖ መቅረት የለበትም። በሥራ መገለጽ አለበት 1ኛ ዮሐ. 3፡8፤ ያዕ. 2፡15-16 ይኸውም ባልንጀራችንን በሥጋና በመንፈሳዊ ሕይወት በመርዳት ይገለጣል።

<u>በሥጋዊ ሕይወት</u>

- ለኑሮ የሚያስፈልገውን ነገር ምግብ፣ ልብስና መጠለያ ማሟላት
- መብቱ እንዲጠበቅለት ማድረግ
- ጉዳት እንዳይደርስበት መጠንቀቅና መከላከል

<u>በመንፈሳዊ ሕይወት</u>

- በጸሎት ማሰብ 2ኛ ጢሞ. 1፡3
- በጥሩ ተምሳሌትነት ወደ ቤተ እግዚአብሔር ማቅረብ ማቴ. 5፡16፤ 1ኛ ጴጥ. 5፡3
- በመንፈሳዊ ምክር ማነጽ ሮሜ. 12፡8

በዚህ ብቻ ሳይወሰን በፍቅር ለሌላው እራስን አሳልፎ እስከመስጠት ድረስ ሊቀጥል ይገባዋል። የፍቅር የመጨረሻው ደረጃ ይሄ ነው። ጌታችን ነፍሱን ስለወዳጆቹ አሳልፎ ከመስጠት የሚበልጥ ህግ ለማንም የለውም ብሏል። ዮሐ. 15፡13

<u>እንደራስህ ውደድ</u>

ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ የሚለው ትዕዛዝ ለባልንጀራችን የሚኖረን የፍቅር መጠን ምን ያህል መሆን እንደሚገባ ያስረዳል። ራሳችንን በምንወድበት መጠን መውደድ አለብን። የገዛ ሰውነቱን የሚጠላ የለም ኤፌ. 5፡30 በክርስትና ሃይማኖት የክርስቶስ አካል እንደሆነና እያንዳንዳችንም ብልቶች እንደሆንን ተገልጧል፡ 1ኛ ቆሮ. 12፡27

ስለዚህ አንዱ አንዱን አታስፈልገኝም ሊለው አይችልም። የራሱ ብልት ነውና። ሌላው ቢቸገር ቢታመም ቢደሰት የኛም ሊሆን ይገባል። ሌሎች ሊያደርጉልን የምንፈልገውን ነገር ሁሉ ለባልንጀራችን በማድረግ በተግባር እንግለጸው። ማቴ. 7፡12

<u>አንቀጸ ብፁአን</u>

አንቀጸ ብፁአን የተባለውን ትምህርት ያስተማረው ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ትምህርቱም የሚገኘው በማቴዎስ ወንጌል ከምዕራፍ 5-7 ድረስ ነው። አንቀጸ ብፁአን የተባለውም ትምህርቱ በብፁአን አዋጆችን ስለሚጀመር ነው። አንቀጸ ብፁአን የተራራው ስብከትም ይባላል። ምክንያቱም ጌታ ትምህርቱን ሲያስተምር በእስራኤል ሰሜን በጥብርድያኖስ ባህር አጠገብ በጥፍርናሆም አካባቢ በሚገኘው ሁለት ማይል ከፍታ ባለው ተራራ ኮረብታ ላይ ስለሆነ ነው። ማቴ. 4፡1-11

ይህ ትምህርት የሐዲስ ኪዳንን ሕግ የያዘ ነው። የብሉይ ኪዳን ሕግ በተራራ ላይ እንደተሰጠ ሁሉ የሐዲስ ኪዳንም ሕግ በተራራ ላይ ተሰጠ። የሐዲስ ኪዳን ሕግ በፊደል ሳይሆን በመንፈስ የሚመራ ነው። ስለዚህ የመንፈስ ሕግ ይባላል። ለክርስቲያን የሕግ ሁሉ ፍጻሜ ፍቅር ስለሆነ ሕግጋቱን የሚፈጽመው በፍቅር ተገዶ ነው። እንዲያውም ከታዘዘው በላይ አትርፎ መልካምን ይሠራል። በዚህም ምክንያት የሐዲስ ኪዳን ሕግ ትሩፋት ይባላል። በብሉይ ኪዳን ሙሴና ነቢያት እግዚአብሔር እንዲህ ይላል በማለት ሕግን ያስተምሩ ነበር ጻፎችና ፈሪሳውያንም